## ዋዬ ዋዬ ዋዬ፤ ጉሮ ወሸባዬ!

ኬትኛው ነህ አነተ ከየቱ ወገን ነህ፤

ሞተና አረፈው ወይንስ ሞተብህ፤

ዋዬ ዋዬ ዋዬ ዋዬ ዋዬ ዋዬ!

ወይስ ልትለው ነው ጉሮ ወሸባዬ?

መሞትስ አይቀርም ሁሉ ሰው ይሞታል፤

ስጋው ታበቃለች ነፍሱ ይቀጥላል፤

በምድር ፍርድ ጠፍቷል፤

በላይ ይቀጥላል፤

ሀዘንም ደስታ ድብልቅልቁ ወጥቷል።

ከቶ የት ተገኘ ሁሉን የሚያስደስት፤

ሁሉን የሚያስለቅስ በነበረ ህይወት፤

እኛን የገረመን በመጨረሻ ለት፤

በቅራሌ ኑሮ በቅራኔ መሞት፤

ደግሞ እንደገና ሊያስለቅስ? ሊያሰደስት?

የቸገረ ነገር የጠፋ ለመላ፤

እርሱ በገደለ በጠጣ በበላ፤

እኛን መሞገቱ ከሞተ በሁዋላ፤

ምንም እንደማያውቅ ደግሞም እንደሌላ፤

እዘኑ አልቅሱ ሳቁ በሚል ፌዝ፤

ተረስቶ ተዳፍኖ ያ-ሁሉ መዘዝ!

ሰው ሲያልፍ ልማድ ነው "ነፍስ ይማር ነፍስ ይማር"፤

ከቶ ምን ፈየደ የልቡን ቢናገር፤

አለቀ አከተመ ፍርድን ለእግዚአብሔር፤

ብለን እንተውወ ስራው አይቀበር፤

ታሪክ ይተንትነው ለትውልድም ያኑር።

የሁዋላ የሁዋላ እውነት ስትወጣ፤

ወገን እንዳልሆነ ቀንደኛ ባላንጣ፤

ደም እነደምትጮህ ከየመቃብሩ፤

ፍርድማ ቀልጣለች የለች በአገሩ፤

የሞተ ተጎዳ አገርም ድንበር፤

ታሪክም ውል ፈሯን ሳለ እንዳልነበር፤

ትረሳው እንደሆን አይረሳን እኛን፤

የደረሰብንን ደግሞም የሆንነውን።

ፍ.አ

08 21 2012